በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ቅድመ ጋብቻ

## ክፍል 3

## ጋብቻ ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12:30 – 1:30 ምሽት
ታህሳስ ፳ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# መግቢያ

- በሚያሳዝን መልኩ ባለንበት ክፍለ ዘመን ጋብቻ/ትዳር በአደጋ ውስጥ ይገኛል፡፡
- ጋብቻን በዘዴ አጣምሞና አመሳስሎ ለመተርጎም የሚሞክሩ በርካታ ጥፋቶች እየታዩ ነው፡፡
- ላለፉት ሃምሳ ዓመታት የታዩት በጾታ ስም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ልቅ የሥጋ ፈቃድ መፈጸሚያ ፊልሞችና ሥዕሎችን፤ መወሰን የሌለበት የግብረሥጋ ግኑኝነትን፤ ያለ ሕግ ወይም ያለ ሥርዓት የሚፈጸም አብሮ መኖርንና ፊቺን በከፍተኛ ሁኔታ ከማስስፋፋቱም በላይ የትዳርን/ጋብቻን ሕይወት አዳክሟል፡፡
- አንዳንዶችም የጋብቻን ትክክለኛ ትርጉም ፈጽሞ የሚያጠፋ ትርጓሜ እየፈጠሩ ነው፡፡

## በዓለማችን ጋብቻን የገጠሙ ችግሮች ታሪክ

- በፍቺ #አብዮት; የተነሳ ጋብቻ ለዕድሜ ልክ መሆኑ እየተቃለለ ይገኛል፡፡ ዛሬ ከግማሽ ያላነሱ ጋብቻዎች በፍቺ ይጠናቀቃሉ፡፡
- ልቅ በሆነ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ዓመፃ የተነሳ ግኑኝነትን ለማድረግ ብቸኛ መንገድ የሆነው በጋብቻ መኖር ተንቋል፡፡ ቅድመ ጋብቻ ግኑኝነት፤ ጊዜያዊ የኮንትራት ዓይነት ስምምነት.. ድንበር እንዲጣስ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡
- አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚለው ትክክለኛው (ተፈጥሮአዊው) የጋብቻ ትርጉም በግብረ ሰዶማውያን የ#ጋብቻ; መብት ጥያቄ የተነሳ እጅግ በመፈተን ላይ ይገኛል፡፡
- ከዚሁ ጎን ለጎን የማኅበራዊ ሳይንስ ጥናቶች ጋብቻ ለወንዶች፤ ለሴቶችና ለልጆች ያለውን ጠቀሜታ ከፍተኛነት ሳይደብቅ በሰላማውያን ባልና ሚስት የሚመራ ቤተሰብ ደስተኛ፣ ጤናማ፣ እጅግም የተሟላላቸው ባለጠጋ እንደሆነ ያብራራል፡፡
- *ታዲያ ጋብቻን ለመታደግ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? አስቀድመን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ ይገባል፡፡*

# <u>አስቀድመን መመለስ የሚገባን መሠረታዊ ጥያቄዎች?</u>

1. ጋብቻ ለምን አስፈለገ?

- በእግዚአብሔር የተፈጠረ ስለሆነ። <u>ዘፍጥ. 2 * 18 — 24።</u>
- በቀድሞ ተፈጥሮአችን ለሁላችን የተሰጠን ስለሆነና የእግዚአብሔር ለሆንን ሁሉ ልዩ ትርጉም እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያስረዳን።

*<u>የጋብቻ ሥነ መለኮታዊ ትርጉም</u>*

*<u>ጋብቻ ምስጢረ ሥላሴን የሚያስረዳን ነው።</u>*

- ሥላሴ በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ ናቸው ብለን እናምናለን። በአካል ሥስትነታቸው ለእያንዳንዳቸው የተለየ አካል ያላቸው ሲሆን በአንድነታቸው ደግሞ ያለመለያየት ይኖራሉ።
- ይኽ አንድነትና የተለየ አካል ሰውን በአምሳሉ ለመፍጠሩ ማስረጃ ነው። እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል የሚመሳሰልበትና የሚለያይበት እንዳለው አድርጎ ፈጠረው።
- አዳም ለእንስሳት ሁሉ ስም ቢያወጣም የሚመስለውን ግን አላገኘም። ከአዳምም ከራሱ አጥንት ወስዶ ከአዳም ግን የተለየች አድርጎ ሴትን ፈጠረ።
- የሰው ዘር ያለወንድና ያለ ሴት ፈጽሞ የተሟላ አይሆንም። በጋብቻም ሲጣመሩ አንድ ይሆናሉ የእግዚአብሔርንም አንድነት ያስረዳሉ።

*ሥነ መለኮታዊ ምሳሌ ለጋብቻ*

1. ብሉይ ኪዳን
   - በብሉይ ጋብቻ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ለነበረው ግኑኝነት ምልክት ነበር።
   - ሌሎችን አማልክት ማምለክ እንደ አመንዝራነት ለእስራኤልም ያለሕግ እንዳገቡት ባል/ሚስት ይቆጠር ነበር።

#እግዚአብሔርም በንጉሡ በኢዮስያስ ዘመን እንዲህ አለኝ። ከዳተኛይቱ እስራኤል ያደረገችውን አየህን? ወደ ረዘመው ተራራ ሁሉ ከለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች ሄደች በዚያም ጋለሞተች። ይህንም ሁሉ ካደረገች በኋላ። ወደ እኔ ትመለሳለች ብዬ ነበር ነገር ግን አልተመለሰችም አታላይ እኅትዋም ይሁዳ አየች። ከዳተኛይቱም እስራኤል ስላመነዘረች ስለዚህ ፈትቻታለሁ የፍችዋንም ወረቀት ሰጥቻታለሁ አታላይ እኅትዋ ይሁዳ ግን እንዳልፈራች እርስዋም ደግሞ ሄዳ እንደጋለሞተች አየሁ።; <u>ትንቢተ ኤርምያስ 3 * 6 -8።</u>

# አስቀድመን መመለስ የሚገቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች? ...

2. ሐዲስ ኪዳን
 - በሐዲስ ኪዳን ጋብቻ በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል ላለው ግኑኝነት ምልክት ነው፡፡
 ኤፌሶን 5 * 21 — 23 ፤ ራዕይ 19 * 7 - 9

*ጋብቻ የእግዚአብሔርን ዓላማ የሚያስረዳ ወይም የሚያሳይ ነው*

1. ብሉይ ኪዳን
 - ጋብቻ በብሉይ ኪዳን በምድር የተዘራ የእግዚአብሔር ዘር ነው፡፡
2. ሐዲስ ኪዳን
 - ጋብቻ በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን መንግሥት በወንጌል አማካይነት በምድር ለማስፋት ታላቁን ሚና የሚጫወት ነው፡፡
   - ተጋቢዎቹ በክርስትና ሃይማኖት እየኖሩ በሕይወታቸው ምስክር ስለሚሆኑ፡ 1ኛ ጴጥ 3* 1-6
   - ልጆችም የሃይማኖታቸውን መንገድ ጠንቅቀው ስለሚያድጉ፡፡ ኤፌ 6 * 4 ፤1ኛ ቆሮ 16* 19

2. የጋብቻ ዓላማ ምንድር ነው?

- *ከጋብቻ ዓላማዎች አንዱ መረዳዳት ቢሆንም መረዳዳቱ በተቃራኒ ጾታ መካከል ብቻ ያለ ነው፡፡* አንዳቸው ከሌላው የሊላቸውን ያገኙ ዘንድ ጋብቻ በወንድና ሴት ነውና፡፡ ዘፍጥ. 2 * 18 — 24፡፡
- *የሰውነትን ፈቃድ ማስተካከል*
  - ከጋብቻ ውጪ የሆኑ ግኑኝነቶች ሁሉን ሊጎዱ የሚችሉበት ጎን አላቸው፡፡ 1ኛ ቆሮ 6 * 12-20
  - ከጋብቻ ውጪ የሆነ ግኑኝነት ለወላጅ አልባ ሕጻናት መፈጠር፣ በግብረ ሥጋ ለሚተላለፉ በሽታዎች መስፋፋት ምክንያት ይሆናል፡፡
  - የሥጋ ፈቃድም እስከ ግብረ ሰዶማዊነት አይደለም፡፡ ግብረ ሰዶማዊነት ከሕገ እግዚአብሔር ውጪ ፈቃድን ከተቃራኒ ጾታ ጋር መፈጸም ሲሆን አልፎም በአንድ ያልተወሰነና መጠን ከሌላቸው ጋር መባለግ ነው፡፡ እንደ መብት እንኳ መጋባታቸው ቢፈቀድ በአንድ ስለመወሰናቸው ዋስትና አይሰጡም፡፡

# አስቀድመን መመለስ የሚገቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች? …

- ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው በሚፈልጉት መንገድ ይኸን የሥጋን ፈቃድ መፈጸም ቢፈቀድላቸው ወደፊት የሚከተሉትን ይቀጥላሉ ብለን እንጠብቃለን፡፡
  - በሕግ አግብተው ከሚባልጉት ይልቅ ጥቂት ግብረ ሰዶማውያን የጋብቻን ኃላፊነት መወጣት የሚፈልጉ አለመሆናቸውን
  - ይልቁኑ ወንድ ግብረ ሰዶማውያን ለጥቅማቸው ሲሉ ያልጸናና የግብረ ሥጋ ግኑኝነት መተማመን የሌለበት የተፈቀደውን የአንድ ወንድ ለአንድ ሴት ግኑኝነት ለሚቀጥሉ መሆናቸው
  - የግብረ ሰዶማውያኑን አእምሮ ከመለወጥ ይልቅ ሰው ስለጋብቻ ያለውን ጤናማ አስተሳሰብ በማጣጣል የትክክለኛውን ጋብቻ ሚናና አቅም ማዳከም

- *ዘርን መተካት (በምድር መብዛት)*
  - ዘፍጥ 1* 27 -28፡፡
  - የሰው ዘር በምድር ላይ እንዲበዛ ወንድና ሴት በጋብቻ ተጣምረው መኖር ይኖርባቸዋል፡፡
  - አንዳንዶች በመካንነት ሌሎች ደግሞ በዕድሜ የተነሳ መውለድ መራባት አይችሉም፡፡
  - ይሁን እንጂ ፈጽመው ለመውለድ ካለመፈለግ የተነሳ የሚቀራረቡ ግብረ ሰዶማውያን ይህን ዓይነት ሰዎች መጋባታቸው ጥፋት እንዳልሆነ ይጠቅሳሉ፡፡

# ጋብቻን መታደግ የምንችለው እንዴት ነው?

-ቀጥለው የተጠቀሱት ጋብቻን ለመታደግ በየግላችን መከተል የሚገቡን መንገዶች ናቸው፡፡

1. የራሳችሁን ጋብቻ ጤናማነት ጠብቁ፡፡
   - ለብቻችሁ የምትሆኑበት ጊዜ ይኑር፡፡
   - ከትዳር ጓደኛችሁ ጋር በግልጽ በጋብቻችሁ ውስጥ ስላለው ችግር ተወያዩ፡፡
   - ከፍ ያለ ችግር ያለባችሁ ከሆናችሁ የንስሐ አባቶቻችሁንና በትዳር ጸንተው የኖሩትን ምክር ጠይቁ፡፡

2. ልጆቻችሁ ጋብቻን እንዲያከብሩ አስተምሯቸው፡፡
   - ከጋብቻ በፊት ከሚኖር የግብረ ሥጋ ግኑኝነት እንዲታቀቡ አስተምሯቸው፡፡
   - በወንድና በሴት፣ በባልና በሚስት፣ በእናትና አባት መካከል ለሚኖር ጤናማ ግኑኝነት ምሳሌ(Model) ሁኑአቸው፡፡

የሚከተሉት ደግሞ ከቤተክርስቲያን ልናገኛቸው የሚገቡ ናቸው፡፡

1. ከመጋባት በፊት በቂ የቅድመ ጋብቻ ትምህርት ማግኘት፡፡

2. በጋብቻቸው እገዛ ለሚያስፈልጋቸው መስጠት፡፡

3. በጋብቻቸው ጸንተው ለረጅም ዓመታት የኖሩ ለተጫጩ፤ አዲስ ለተጋቡና ለተሳሰቡ ሁሉ ምክር ሊሰጡ የሚችሉባቸውን መርሐ ግብሮች መንደፍ፡፡

# ጋብቻን መታደግ የምንችለው እንዴት ነው?

ቀጥለው የሚገኙት ደግሞ እንደ አገሪቱ ዜጎች ጋብቻን ለመታደግ ወይም ለመጠበቅ የምንከተላቸው መንገዶች ናቸው፡፡

1. ሕዝቡና የሕዝብ ተመራጮች ጋብቻንና ቤተሰባዊ ሕይወትን በመደገፍ እንዲቀጥሉ ኃላፊነት የሚሰማቸው ባለትዳሮች የሚያበረታቱበት ወዳጅነት የተሞላበት ፓለቲካ እንዲያራምዱ ማሳሰብና ማስፈጸም፡፡

2. በውሃ ቀጠነ መፋታት ፈልገው ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡትን በተመለከተ የሕግ ተወካዮች #ለመፋታት በማያበቁ; ምክንያቶች ፊቺን የሚከለል ሕግ መኖር የሚችልበትን #የማይፈርስ ቃል ኪዳን; ጋብቻ ሕጎች እንዲረቀቁ ማድረግ በሚችሉበት መንገድ መመካከር፡፡ (Check and Balance)

3. ከጋብቻ በፊት ከግብረ ሥጋ ግኑኝነት መታቀብን የሚያበረታቱ የጋብቻና የቤተሰብ ሥርዓት ትምህርቶች እንዲዘረጉ ትምህርት ቤቶችንና የሚመለከታቸውን ተቋማት መጠየቅ

4. አሁን እንዳለው መንግሥታዊ የሆኑ የሕግ አካላት ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት ብቻ መካከል የተወሰነ ሆኖ ሕጋዊ ከለላ አግኝቶ እንዲቀጥል ማንኛውንም አስተዋጽኦ ማድረግ፡፡

5. አሁን እንዳለው ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት ብቻ መካከል የተወሰነ ሆኖ ሕጋዊ ከለላ አግኝቶ እንዲቀጥል ለሚያደርጉ አካላት በሙሉ የሚቻለንን እገዛ ማድረግ፡፡

6. አሁን ካለው በአንድ ወንድና በአንድ ሴት ብቻ መካከል የተወሰነ የጋብቻ መንገድ ውጪ ያሉ ሂደቶችን ሁሉ መቃወምና ድምጽም ሲያስፈልግ ተቃውሞ ድምጽ መስጠት፡፡

7. ሁሉም ወገን ከላይ በተነሱት ጉዳዮች ዙሪያ በአንድነት መሥራት ይችሉ ዘንድ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች ፣ በመንግሥት ሚዲያዎችም መልዕክቶቻችንን ማስተላለፍ፡፡

# ማጠቃለያ

- በሚያሳዝን መልኩ ባለንበት ክፍለ ዘመን ጋብቻ/ትዳር በአደጋ ውስጥ ቢገኝም፤

- ጋብቻን በዘዴ አጣምሞና አመሳስሎ ለመተርጎም የሚሞክሩ በርካታ ጥፋቶች እየታዩ ቢሆኑም፤

- ሳለፉት ሃምሳ ዓመታት የታዩት በጾታ ስም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ልቅ የሥጋ ፈቃድ መፈጸሚያ ፊልሞችና ሥዕሎችን፤ መወሰን የሌለበት የግብረሥጋ ግኑኙነትን፤ ያለ ሕግ ወይም ያለ ሥርዓት የሚፈጸም አብሮ መኖርንና ፊቺን በከፍተኛ ሁኔታ ከማስስፋፋት በላይ የትዳርን/ጋብቻን ሕይወት በማዳከም ትርጉሙን ለማዛባት ቢጥሩም፤

_- አሁን ክርስቲያኖች ሁሉ በአንድነት ስለጋብቻ መናገር፤ መጻፍ፤ መወያየት … ካልቻልን ትክክለኛው ጋብቻ በሚቀጥለው ትውልድ እየጠፋ መሄዱ የማይቀር ነው።_

_- ስለ እውነተኛው ጋብቻ መናገሪያና ጋብቻን መታደጊያው ጊዜ አሁን ነው።_

_- አሁን እንናገር ዘወትርም እየተናገርን ሰላማችንን እንጠብቅ።_

ይቀጥላል...

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።